# አለገና ገና

ታደለ መኩሪያ

ቀደም ብላ ጥሩነሽ ዴባባ በአሥር ሺ ሜትር በማሸነፏ ከኢትዮጵያ አልፋ አፍሪካን በወርቅ አስጊጣ ስለነበር፤ ለወንዶቹ አሥር ሺ ሜትር ኃይሌ ገብረ ሥላሴ ኪኒሳ በቀለና ስለሺ ስህን ለውድድሩ ሲዘጋጁ አለገና ገና በማለት እስፖርተኞቻችን ያቀነቀኑላቸው ነበር። ቴወድሮስ ካሣ ወይም ቴዲ አፍሮ ቀደም ባሉ ኦሎፒኮች እስፖርተኞቻችን ሲያሸንፉ የሚያቀነቅነውን 'ድል ናፍቀናል' ይመስላል። ዛሬ ደግሞ በጭልምተኞች ጭለማ ቤት ባይዘጋበት ምን ያሰማን እንደነበር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ልተወው።

ለሁሉም እኩል በሆነው የኦሎፒኩ ውድድር የሃገር ልጆች አሸንፌው ስንደቃ ዓለማችን ከፍ ብላ ስትውለበለብ ስናይ፤ ያስደስታል፤ተስፋን የቀረጠን መንፈስ ያነቃቃል፤ለሕዝብ የእምርታን ለውጥ ለማምጣት የተስፋን ጮራን ይፈነጥቃል፤እያንዳንዱን ዜጋ ለሃገሬ ለራሴ ምን ሰርቻለሁ? ምንስ ሰርቼ በዚህ ዓለም መኖሬ አስመሰክራለሁ፤ በልጅ ልጆቼስ እንዴት እጠቀሳለሁ የሚለውን አዕምሮን የሚሸነቁጠውን ጥያቄ ይጋብዛል።

የኦሎፒክ ውድድር በሃገራችን ሕዝብ ላይ የሚያመጣውን የስነልቦና ለውጥና ለለውጥ መነሣሣት ከመግለፄ በፊት ሃያ ዘጠነኛው ኦሎቲክ ስለአዘጋጀችው ቻይና ልተርክ።

የቻይና ሕዝብ በኮሚንስቱ ማኦ ሴንቱግ መሪነት የካፒታሊስት አቀንቃኝ የነበረውን ኮሚተንግን ድል አድርጎ እ ኤ አ 1949 ዓ ም የኮሚኒስትን ርዕዮተ ዓለም የሚከተል መንግሥት አቋቋመ። የዛሬ ስልሳ ዓመት መሆኑ ነው።በቅርቡ የወያኔ መንግሥት ግባ ተመሬቱን የፈጸመበትን የአንጋፋውን የኢትዮጵያን መምህራን ማሕበር ዕድሜ ማለት ነው።

ዛሬ የዓለም ሕዝብ ያሸረገደላትና ሰማይ የጠቀሰ አድናቆትን ያጎናጸፋት ቻይና በኮሚንስትነቷ ከምዕራቡ ዓለም የተገለለች ነበረች። ያም ሆኖ ኢትዮጵያ ከቻይና ዋና ተፃራሪ ከነበረችው አሜሪካ የጠበቀ ግንኙነት ቢኖራትም የቀድሞው ንጉሥ ሐፄ ኃይለሥላሴ ቻይናን ለመጎብኘት የዲፕሎማ ሲ ትስስር ለመፍጠር ችለዋል።ይህንን ለማድረግ የማንንም ፍቃድ አልጠየቁም። ከዚህ ልንማር የሚገባን መሪዎቻችን ሆኑ ሕዝቡ የአዕምሮ ነፃነት እንዳላቸው ነው። ለአንዳንዶቻችን ኢትዮጵያ በነፃነቷ ተከብራ የኖረች ሃገር ናት ሲባል የጆግራፊዋ መልካዓ ምድሯ ብቻ ይመስለናል፤ ዋናው ግን በአዕምሮአችን በነፃነት ያለ ተጽኖ ማሰብን ያካተተ መሆኑ ይዘነጋናል።

ቻይና ምንም እንኳን ከምዕራቡ አገሮች ተገላ ብትቀይም ጠንክራ በሕብረት በመሥራት ምጣኔ ሐብቷን አሳደገች።በእስፓርቱም የጠረጴዛ ኳስን እንደፓስፖርት ተጠቅማ የምዕራቡን አገራት በር አስከፈተች። ይሂው ዛሬ በማንኛው አስፖርት የዓለም ቁንጮ ሆነች።

ዛሬ ኃይሌ ገብረ ሥላሴ ታላቁ ሩጫ ብሎ የጀመረው ለሌሎቹም የእስፓርት ዓይነቶች ያዘጋጀን ይሆን? ያለችሎታና ያለሞያ ጣልቃ ገብነት ከቆመ ኃይሌ እንዳለው ይቻላል።

የእስፓርተኞቻችን በኦሎፒክ ማሸነፍ በሕብረተሰባችን ላይ ያመጣውን የሰነ ልቦና መነሣሣት የለውጥ ፍለጋ ብዙ ዓመት ወደኋላ ተመልሼ ልጠቁም።

እ ኤ አ 1960 ዓም ነሐሴ ወር ነበር ። በከተማችን ሬዲዮ ያላቸው ከአስር አይበልጡም። ሬዲዮ የሚሠራው የመኪና ባትሪ በሚያክል ስለነበር ኃይሉ ከደከመ መለወጡም ወጪ ይጠይቃል።አንዳንድ ግለሰቦች ኃይሉ ሲደክም ፀሐይ ላይ ያሰጡታል።እንደልብ ዜና አናገኝም። በሬዲዮ ዜና ያዳምጡም ከነበሩ አላካፈሉንም። እንደወትሮው በሳምንት ሦስቴ በከተማችን የሚያርፈው ዲሲ 3 አይሮኖላን ነበር፤ አበበ ቢቂላ በሮማ ከተማ በማራቶን ሩጫ አሸናፊ መሆኑን ያበሰረልን ። ይህቺ ከሁለት ሺ ሕዝብ በላይ የማይኖርባት ከሱማሌያ ጠረፍ ብዙም የማትርቅ ከተማ ሕብረተሰብ በደስታ ፈነደቀ።እናቶች ሳይቀሩ ለቡናቸው ሲሰባሰቡ የመጫወቻቸው ርዕስ የአበበ ቢቂላ ጅግንነት ሆነ። የማራቶን ሩጫ የድል ማብሰሪያ አርማ መሆኑን የተረዱት ጅንራል መንግሥቱ ንዋይና ወንድማቸው ገርማሜ ንዋይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሥረዓት ለውጥ ማራቶኑን ለማድረግ ተነሣሱ።የአበበ ቢቂላ

ማራቶን በነሐሴ የነጅንራል መንግሥቱ ማራቶን ከአራት ወር በኋላ በታህሳስ ሶስት ነበር። ይሄው ዛሬ እንደምናየው የሥልጣን ጥመኞች የማራቶኑን ሩጫ በሜትር አስቀሩት።

እ ኤ አ 1964 ዓ ም ለሁለተኛ ጊዜ አበበ ቢቂላ በጃፓን ቶኪዮ በማራቶን አሸንፎ ስንደቃ ዓለማችን በኦሎፒክ አንባ እንደትውለበለብ አደረገ። አበበ በቂላ የኢትዮጵያ ዜጋ ብቻ ሳይሆን የዓለም ዜጋ ሆነ። አበበ በነሐሴ አሸንፎ አሁንም በታህሣሥ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች 'መሬት ለአራሹ' መፈክር ይዘው አደባባይ ወጡ። ጅንራል መንግሥቱ በሐፄ ኃይለ ሥላሴ ከፈጠረባቸው የዙፋን መናጋት የተማሪዎቹ ደግሞ እጅግ አስቆጣቸው እዘጋዋለሁ እስከማለት አደረሳቸው።

የሚገርመው ግለሰቦች በጥረታቸው በየጊዜው ከዓለም ዙሪያ ከመጡ እስፖርተኞች ጋር እየተወዳደሩ ሃገራችንን ሲያስጠሩ፣ በጋራ ከአርባ ዓመት በፊት የተነሣንበትን በአዕምሮችን በነፃነት ማሰብ፣ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት ማቋቋም 'የመሬት ላአራሹን'ጥያቄ መመለስ አልቻልንም።

በግላቸው በጊዜአቸው አበበ ቢቂላ ማሞ ወልዴ ምሩጽ ይፍጠር መሐመድ ከዲርን ለሕብረተሰባችን ያበረከቱትን ለታሪክ ልተወውና በዘመናችን ስለበቀሉት እፖርተኞች ልተርክ።

እ ኤ አ 1992 ነበር በእስፔን ባርሶሎና የኦሎፒክ ዝግጅት እንደሚከናወን በመገናኛ ብዙሃን ብዙ ይነገራል። ሃገራችን በደቡብ ኮሪያ በአሜሪካ ሎሳጀለስ ተካፍላ ሰላልነበር የመመልከት ስሜቴ ቀንሷል። ከሃገርም የሚመጣው ዜና ተስፋ የሚያስቆርጥ ነበር። ድርግ ተለውጦ ኢትዮጵያ ከጦርነት ወደሰላም ትሸጋገራለች የሚለው ተሰፋው የጨለመ ነበር። ወያኔ ሕውሃት ሃገሪቱን በዘር ከፋፍሎ አበበ ቢቂላ በሩጫ ዘራይ ደርሰ በጎራዴ ያበረከካትን የጣሊያን ካርታ በሥራ ላይ የሚየውል ድርጅት በሃገራችን ተፈጠረ።በዘር ፖለቲካ ሃገራችንን ጃርት የቦረቦረው ዱባ አስመሰላት። የምንኮራበት የሶስት ሺ ዘመን ታሪካችን የመቶ ዓመት ታሪክ ተባለ፣ ወድቃ በተሰሣችው ሰንደቃ ዓለማችን ሲባል ወንዝ እንኳን ይቆማል የተባለላት ብጣሽ ጨርቅ ተባለች። በዚህ አኳኋን ምን ዓይነት ዜጋ ይህን ጥሶ ሃገሩን ያስጠራል በማለት ተስፋ ቆርጬ ኦሎፒክን ለመከታተል ፍላጎቱም አልነበረኝም።

ክፍል የምንጋረው የነጭ ጓደኛዬ ከጥራጊ ውስጥ ያመጣት ጥቁርና ነጭ የምታሳይ ቴሌቪዥን በመኖሪያ ክፍላችን ትገኛለች። ለዜና ብቻ እንጠቀምባታለን። እንዳጋጣሚ ዜና ስከታተል የኦሎፒክ መክፈቻው ቀን ኖሮል።እግር መንገዴን ከዓለም ዙሪያ የመጡ እስፓርተኞች ሰማቸው እየተጠራ ሲያልፉ ባልሳሳት ከጁቡቲ ቀጥሎ የእኛ እስፖርተኞች አለፉ።የምጠብቀው ግርማ ሞገስ አለነበረም። ለሙዳ ወደ ድሬ ሽሁሴን የሚጓዙ ገሪባዎች ይመስላሉ። ይበልጥ ቆሽቴ አረረ፣ ከመኝታ ቤቴ ገብቼ ተኛሁ።

ከቀናት በኋላ አሁንም ለዜና ቴሌቪዥን ሰከፍት 'Tulu of Ethiopia'

እያለ አስተዋዋቂው ሲጣራ ሰሜቴን ሰለሳበው ተመቻችቼ ቁጭ አልኩኝ። ቱሉና ኢትዮጵያ የሚለው ሰም ተደጋግሞ ሲጠራ በውስጤ ትልቅ ኃይል ተሰማኝ። ሲቃ ተናነቀኝ ዐይኔ እንባን አዘለ። በአሸናፊነት ወጥታ ደራርቱ ቱሉ ሲባልና ሰንደቃ ዓላማችንን ስታውለበልብ 'ሃገሬ በሕይዎቷ አለች' ብዬ ከጣሪያው በላይ ጨውኩኝ። እኔም ከመቀብር እንደተነሳ ሰው ተሰማኝ።

ስሜቴን ለመግለጽ ብዕሬን አነሳሁ። 'ሐርከ ፉኔ ደራርቱ' በማለት ግጥሜ ለኢትዮጵያ ሪቪው ላኩላቸው እነርሱም አወጡልኝ።ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስፖርተኞቻችን አላሳፈሩንም። አበበ ቢቂላ የለውጥ ሐዋሪያ እንደሆነ ሁሉ ሰማቸውን በመሉ ጠርቼ ሰለማልጨርሰው የምርጫ 2005 ከኦሎፒክ 2004 በግሪክ ከተካሄደው የቀጠለ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።ከቤንጅጉ 2008 ኦሎፒኩ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በ1960 ዓ ም ያነሣው ጥያቄ መልስ ያገኝለት ይሆን? ወይስ ለልጅ ልጆቹ ባርነትን ረሃብን ትቶ ያልፏል።

እስፖርተኞቻችን እንደ ዲሞክራት ምርጫ በየአራቱ ዓመት በእናንተ ድል እንድንደሰት ሰላደረጋችሁን ምስጋና ይግባችሁ።

ታደለ መኩሪያ